የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፰ ቀን ፪ሺ፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 3
ADDIS ABABA 17th December, 2009


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፱/፪ሺ፪ ዓ.ም

ለሦስተኛው የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፩፻፯


**CONTENTS**


**Proclamation No. 659/2009**

International Development Association Financing Agreement for Productive safety net APL III Project Ratification Proclamation Page 5107


## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፱/፪ሺ፪

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሦስተኛው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፹፫ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሰማንያ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፴ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፱/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 659/2009.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 83,100,000 (eighty three million one hundred thousand Special Drawing rights) for financing Productive safety net APL III Project was signed in Addis Ababa on the 30th day of October 2009;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Represent - atives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Convention at its session held on the 1st day of December, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Productive safety net APL III Project Ratification Proclamation No. 659/2009."


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በአለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፴ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው የብድር ቁጥር 4666-ET እና የእርዳታ ቁጥር H529–ET ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፫ሚሊዮን፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሰማንያ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፰ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Financing Agreement Loan No 4666-ET and Grant No. H529-ET signed in Addis Ababa on the 30th day of October 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified;

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 83,100,000 SDR (eighty three million one hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of December , 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**